AMHARIC

Fairfax County PUBLIC SCHOOLS
ENGAGE • INSPIRE • THRIVE

# ስኬት በመዋእለ ህጻናት (Kindergarten) የወላጅ ስልቶች



**Fairfax County የህዝብ ትምህርት ቤት (FCPS) ከፍተኛ ጥራት ያለው የህጻናት መዋያ የእያንዳንዱን ልጅ ፍላጎት፣ ዝንባሌ እና የእድገት ደረጃ የሚያሟላ ትምህርት ይሰጣል ብሎ ያምናል። መእለ ህጻናት ለህጻናት በዙሪያቸው ያለውን አለም እንዲያስተውሉ፣ እንዲፈትሹ፣ እንዲሞክሩ እና እንዲመረምሩ እድል ይሰጣል።**

**FCPS ወላጆች የልጆቻቸው የመጀመሪያ አስተማሪዎች መሆናቸውን ይገነዘባል። ይህ ህትመት ለወላጆች ልጆቻቸው ወደ መዋእለ ህጻናት ስኬታማ ሽግግር እንዲያደርጉ እገዛ የሚያደርጉበትን መንግዶች ያሳያል። ወላጆች በራሳቸው ቋንቋ ተጠቅመው ልጆቻቸውን በነዚህ እንቅስቃሰዎች እንዲያሳትፏቸው ይበረታታሉ። ለተጨማሪ መረጃ እባክዎ ይህንን ድህረ ገጽ ይጎብኙ**
**https://www.fcps.edu/academics/elementary-school-academics-k-6/kindergarten**

## የቃል ቋንቋ።
የቃል ቋንቋ ለሁሉም በቃል እና በጽሁፍ ለሚደረጉ ግንኙነቶች ወሰረት ነው።
*ስለዚህ ከልጅዎ ጋር ፡-*

- እርሶ ምን እንደሚያደርጉ እና እነሱ ምን እንደሚያደርጉ ተነጋገሩ።
- ዘፈን/መዝሙር ዝፈኑ/ዘምሩ። የህጻናትንም ዘፈን/መዝሙር ዝፈኑ/ዘምሩ።

## ንባብ ።
ልጆች የማንበብ ባህልን ትምህርት ቤት ከመግባታቸው በፊት ያዳብራሉ። የታተሙ (ለምሳሌ፡- መጽሃፍት፣ የመንገድ ላይ ምልክቶች፣ ኢሜይሎች)
*ከልጅዎ ጋር ሲያነቡ ፡-*

- ታሪክ/ተረት ለማንበብ ወደ ቤተ መጽሃፍት ወይም ወደ መጽሃፍት መሸጫ ቦታ ይሂዱ ።
- ከቤተ መጽሃፍት መጽሃፍ ተዋሱ ።
- ታሪክ/ተረት ለማውራት/ለመፍጠር ቃላት የሌላቸውን ወጽሃፍት እና ሰእሎችን ይጠቀሙ።
- ልጅዎ የራሱን/የራሷን መጽሃፍ ይምረጥ/ትምረጥ።
- ወደ ቃላቱ አመልክቱ እና ምን ማለት እንደሆነ ተነጋገሩ።
- ልጅዎ አንባቢ እንደሆነ/እንደሆነች እንዲያውቅ/እንድታውቅ ያድርጉ ።

## ጽሁፍ መጻፍ።
ልጆች በተለያዩ መንገዶች ጽሁፍ መጻፍን ይለማመዳሉ። በመሞነጫጨር ፣ ስእል በመሳል ፣ የተቀጣጠሉ ፊደሎችን መጻፍ ፣ በራሳቸው ስም ደብዳቤ በመጻፍ ፣ የሚያዩትን ቃላት በመጻፍ ፣ ድምጽን በፊደል አስመስሎ በመጻፍ ምልክቶችን ያደርጋሉ።
*ከልጅዎ ጋር ፡-*

- ስእል መሳልን ፣ ለቤተሰብ እና ለጓደኛ የጽሁፍ ማስታወሻ መጻፍን አበረታቱ።
- ዝርዝሮችን ይጻፉ ።
- ስለሰሩት ሰእል ታሪክ እንዲጽፉ ያድርጉ።

## ሂሳብ።
የልጆች የሂሳብን ግንዛቤ በቤት ውስጥ በሚገኙ እቃዎች በመጠቀም ሊከሰት ይችላል።
*ከልጅዎ ጋር ፡-*

- እንደ ካልሲ ፣ ሴሪያል/ምግብ የመሳሰሉትን እቃዎችን በመለየት።
- አቀማመጥን/ወጥነት በመፈለግ (ለምሳሌ፡- በሸሚዝ ላይ ያሉ ሰንበሮች/ሸንትሮች ፣ የአበባ ቅጠሎች)።
- እቃዎችን ወይም አሻንጉሊቶችን በመቁተር ወይም በመንካት።
- ወደ ሱቅ ሲሄዱ የተለያዩ ሳንቲሞች በየአይነታቸው በመለየት ።

## ሳይንስ።
ሳይንስ ህጻናት በዙሪያቸው ያለውን አለም እንዲፈትሹ እና እንዲያገኙ ያደርጋል።
*ከልጅዎ ጋር ፡-*

- በውጪ ስለሚያዩት ነገሮች ተነጋገሩ።
- ቅጠሎች ፣ እንጨቶች ፣ አበባዎች በየ አይነታቸው መለየት እና ስለ ቅርጽቸው ፣ መጠናቸው እና ሽታቸው መነጋገር።

## ማህበራዊ ጥናት/ጉዳይ።
ልጆች ስለራሳቸው ከማሰብ ወደ በአካባቢያቸው ስለሚገኘው አለም ማሰብ መሸጋገር ይጀምራሉ።
*ከልጅዎ ጋር ፡-*

- የቤተሰብ ታሪክዎን ያካፍሉ። ልጅዎ የቤተሰቡን/ቧን ታሪክ እንዲናገር/እንድትናገር እገዛ ያድርጉ።
- ማህበረሰቡን ማሳወቅ። የእሳት አደጋ መከላከያ ፣ የፖስታ አገልግሎት መስጫ ፣ የፖሊስ ጣቢያ ፣ የማህበረሰብ ማእከል ፣ የመዋኛ ስፍራ እና ስለ ታሪኮች ይንገሩ።

## ቴክኖሎጂ።
ቴክኖሎጂ በአካባቢው ካለ ሌላ የመማሪያ እድል ይሰጣል።
*ከልጅዎ ጋር ፡-*

- በእድሜ መጠን ተገቢ የሆነ ሶፍትወር እና አፕ ያዘጋጁ።
- በመመልከቻው ላይ ምን እንደሚታየው/እንደሚታያት ተነጋገሩ።

## የስሜት መጎልበት ።
ወላጆች ልጆቻቸውን ግልጽ የሆነ እገዳ/ወሰን በማበጀት እና ተገቢ የሆነውን ስነምግባር በማብራራት ሃላፊነት፣ እራስን ችሎ መቆምን እና በራስ መተማመን፣ እንዲማሩ ማድረግ ይችላሉ።
*ከልጅዎ ጋር ፡-*

- ስለ ህጎች እና ስለሚያስከትሉት ቅጣት ተወያዩ። ቀጣይነት ይኑሮት።
- ልጅዎ ስህተት መስራት የትምህርቱ አካል መሆኑን እንዲረዳ/እንድትረዳ ይምከሩ። ምንም እንኳን ከባድ ቢሆንም ደጋግመው እንዲሞክሩ ያበረታቷቸው።
- ልጅዎ የተለያዩ መፍትሀዎችን እንዲፈልግ/እንድትፈልግ (ለምሳለ ፡- “ይህን ለመፈጸም ሌላ መንገድ ማሰብ ትችላለህ/ትችያለሽ?”) በማለት ያበረታቱ።
- ልጅዎ ለአጭር ሰአታት ከእርሶ ተለይቶ/ታ መቆየትን እንዲለማመድ/እንድትለማመድ ለመርዳት በማህበረሰብ መርሃ ግብር ውስጥ ይሳተፉ። ተመልሰው እንደሚመጡ በእርገጠኛነት አሳውቀው ደህና ሁን/ሁኚ ብለው ይሂዱ/ይለዩ ።
- ልብሳቸውን እራሳቸው እንዲለብሱ፣ መጸዳጃ ቤት እንዲጠቀሙ እና እጃቸውን እንዲታጠቡ በማድረግ እራሳቸውን ችለው እንዲቆሙ ማድረግ ይቻላል።

## ማህበራዊ ግንኙነቶችን ማሳደግ።
የማህበራዊ ግንኙነት ልጆች ልክ ከአለም ጋር ሲገናኙነቶችን ሲጀምሩ ይጀምራል። ልጆች በመቻወት እና ሌሎችን በማየት/በማስተዋል በማህበረሰቡ ውስጥ ይማራሉ።
*ከልጅዎ ጋር ፡-*

- ማካፈልን እና ተራ መጠበቅን በሚያስተምሩ ጨዋታዎች እና እንቅስቃሰዎች ይሳተፉ ።
- ልጅዎ ችግር ሲፈጠር ከሌሎች ጋር በመሆን ለችግሮች መፍትሄ በማምጣት ጥረት ውስጥ
  በማገዝ እንዲተባበር/እንድትተባበር ያበረታቱ። (ለምሳሌ፡- “መጫወቻህን/ሽን ሲወስድብህ(ሽ)/ስትወስድብህ(ሽ) እንዳበሳጨህ/ሽ ታዝቤያለሁ”። ይህን ችግር እንዴት መፍታትት የምንችል ይመስልሃል/ይመስልሳል?)

### አካላዊ እድገት።
የአካላዊ እድገትን እና ቅንብርን ለማሳደግ የየቀኑ እድሎች አስፈላጊዎች ናቸው።
*ከልጅዎ ጋር ፡*

- ውርወራን፣ መቅለብን ፣ መምታትን፣ ማንከባለልን ፣ማንጠርን ወይም ኳስን ማባረርን በማለማመድ መጫወት።
- ጨሌ ወይም የልብስ ቁልፍ በክር ማስገባት ወይም የጭማቂ መጠጫ ቱቦ ማጽዳት።
- በአካባቢው ያለውን የመጫወቻ ስፍራ ጎብኙ።

### ተፈጻሚ ተግባራት እና እራስን መምራት። (Executive Function and Self-Regulation)

እንዚህ የአስተሳሰብ ሂደቶች እንድናቅድ ፣ እንድናተኩር እና በስኬት እንድናስታውስ የሚረዱን ክህሎቶች ናቸው። Harvard University Center on the Developing Child ተፈጻሚ ተግባራትን ለማዳበር የሚያስችል መመሪያ አሳትሟል።
https://developingchild.harvard.edu/resources/activities-guide-enhancing-and-practicing-executive-function-skills-with-children-from-infancy-to-adolescence/

## አስደሳች የመማሪያ እንቅስቃሴዎች።

### መለየት።
*እቃዎች፡-* ከተለያዩ የልብስ ቁልፎች ፣ የበር ቁልፎች ፣ ጠጠሮች ድብልቅ

አንድ እፍኝ የሚሆን ዘግኖ መዘርገፍ እና ልጅዎ በቀለም፣ በቅርጽ፣ በመጠን እንዲለይ/እንድትለይ ማድረግ።

### የመጻፊያ መሳሪያዎች ቋት።
እቃዎች፡ ጨው ወይም አሸዋ ፣ ብስኩት መጠቅለያ፣ የቧንባኡአ ማጽጃ ፣ እርሳስ፣ ቀለም መጻፊያ፣ ፖስታዎች፣ የማስታወሳ መጻፊያ ካርዶች ።

ልጅዎ ፊደሎችን ወይም ቃላቶችን መጻፍ ሲጀምር/ስትጀምር እንዲጠቀምባቸው/እንድትጠቀምባቸው የተለያየ እቃዎችን ይስጡ።

### ሂሳብ የእንቁላል ካርቶን ጨዋታ።
እቃዎች፡- የእንቁላል ካርቶን ፣ ማርከር (የቀለም መጻፊያ) ፣ ትናንሽ እቃዎች (ለምሳሌ፡- ዛጎል፣ የልብስ ቁልፍ ፣ ባቄላ ) ።

የእንቁላል ካርቶኑን ጎድጓዳ ውስጥ ከ 1 እስከ 12 ቁጥር ይጻፉበት ። ልጅዎ በእያንዳንዱ ጎድጓዳ ውስት ተመጣጣኝ ቁጥር ያለው እቃ እንዲያስቀምጥ/እንድታስቀምጥ ያድርጉ። (ለምሳሌ፡ በተራ ቁትር 5 ጉድጓድ ውስጥ 5 ዛጎል መቸመር)።

### የመጫወቻ ስፍራ/ሜዳ።
ልጅዎን በተለያየ መንገድ ለመገዳደር የመጫወቻ ቦታ መሳሪያዎችን በመጠቀም እንቅፋቶች ያሉበትን ጉዞ በመፍጠር በዛ ውስጥ እንዲያልፍ/ እንድታልፍ በማድረግ መፈታተን። (ለምሳሌ፡ በመራመድ፣ በመዳህ፣ ማነከስ/በጥፍር መራመድ)።

### እንቆቅልሽ/መገዳደሮች።
ለልጅዎን ችግር ፈቺ ፣ የማስታወስ እና የማቀድ ክህሎቶችን ለማዳበር የተለያዩ እንቆቅልሾችን/መደዳደሮችን ያቅርቡ።

### ማብሰል።
ቁርስ ወይም ትንሽ ምግብ ሲያዘጋጁ ልጅዎ እንዲያግዝዎ/እንድታግዝዎ ይጋብዙ። በምግብ ማብሰል እገዛ ማድረግ እራስን መቆጣጠርን ፣ ማስታወስን ፣ አትኩሮት መስጠትን የቃል ንግግርን ፣ ማንበብን እና የሂሳብ ባህሪያትን ያዳብራል።

## ልጅዎን ወደ ተለያዩ ቦያዎች ይውሰዱ

### ቤተ መጽሃፍት።
Fairfax Countyየህዝብ ቤተ መጽሃፍት – www.fairfaxcounty.gov/library

### መናፈሻ።
Fairfax County Park Authority – www.fairfaxcounty.gov/parks

### የተፈጥሮ ማእከል።
Fairfax County Nature Centers –
https://www.fairfaxcounty.gov/parks/nature-history/parks

### እርሻ።
Frying Pan Farm Park –
www.fairfaxcounty.gov/parks/fryingpanpark/

Cox Farm – www.coxfarms.com

### ቤተ መዘክር።
Smithsonian Institution – www.si.edu

